# የአንድነት ሃይሎች ስብሰባ በቶሮንቶ (ካናዳ)

(ዘጋቢ፡ መላኩ አወቀ)

በኢሕአፓ (ዴ) የቶሮንቶና አካባቢው የድጋፍ ኮሚቴ አባላት አዘጋጅነትና በአንድነት ሃይሎች፤ በሲቪክ ማሕበራትና ታዋቂ ግለሰቦች ትብብርና ግምባር-ቀደምነት ወደፊት ሊመሠረት የታሰበውን ህብረት ዕውን ለማድረግ ጥረት ሲያደርጉ በቆዩትና አሁን እያደረጉ ባሉት አሰባሳቢ የሲቪክ ማሕበራት፤ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮችና ግለሰቦች ትብብር May 14, 2011 በቶሮንቶ ዩኒቨርስቲ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ብዙ ሰዓት የወሰደና አወያይና ተወያይ ልብ ከልብ የተገናኙበት ስብሰባ ተደርጓል።



(ከግራ ወደ ቀኝ: ዶ/ር ወንድሙ መኮንን፤ ዶ/ር ቡሻ ታዓና አቶ መሥፍን ተፈራ)

ስብሰባውንም በእንግዳ ተናጋሪነትና በቁልፍ አወያይነት ህይወት ሰጥተው የመሩት ዶ/ር ወንድሙ መኮንን (ከሎንዶን ፤ እንግሊዝ)፧ አቶ መሥፍን ተፈራ፣ ከኢሕአፓ (ዴ) አመራር ም/ቤትና፤ ዶ/ር ቡሻ ታዓ (ከቶሮንቶ) ሲሆኑ፤ በሰብሳቢነት ደግሞ አቶ ለይኩን ተሾመ (የኢሕአፓ (ዴ) አመራር ም/ቤት አባል) ነበሩ። የዕለቱ ስብሰባም የተጀመረው ለኢትዮጵያ ሰላምን፤ ዴሞክራሲንና ፍትህን ለማስገኘት በግምባር ቆመው ሲታገሉ ለወደቁ ብዙ ሺ ሰማዕታት የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት ተደርጎ ነበር።

ሰብሳቢው የዕለቱን ስብሰባ ዓላማዎች ከገለጹና የአዘጋጁንም ክፍል ጥሪ አክብረው በቦታው የተገኙትን ወገኖች ካመሠገኑ በሁዋላ ስለሦስቱ አወያዮች የትግል ታሪክ፤ ስለትምህርት ደረጃቸውና ስለሚሠሩት ሥራ አንዳንድ ነጥቦችን አንስተውና የአወያይነት ቅደም ተከተላቸውንም አስተዋውቀው ተቀመጡ።

የመጀመሪያው ተናጋሪ አቶ መሥፍን ተፈራ ሲሆኑ፤ እሳቸውም ስለድርጅታቸው የፖለቲካ ፕሮግራም፣ ስለራዕዩና ህብረትን በተመለከተ ይከተል ስለነበረውና አሁንም እየተከተለ ስላለው ፖሊሲ፤ ከዚህ በፊት በድርጅታቸው ግምባር-ቀደም ተሣትፎ፤ ተመሥርተው ስለነበሩት ስብስቦች (ኢዴሃቅ፤ ኢዴሃህና ስለመሣሰሉት)፤ ብርቱና ደካማ ጎኖቻቸው እንዲሁም አሁን እየተደረገ ስላለው አገር-አቀፋዊ የማሰባሰብ ጥረት ድርጅታቸው ስለተጫወተውና እየተጫወተ ስላለው ሚና በስፋት ገልጸዋል። በድርጅታቸው በኢሕአፓ (ዴ) ዕይታም በኢትዮጵያ ያለውን አምባገነናዊ የሆነና ጎጠኝነትን ማዕከሉ ያደረገን የህወሀት/ኢሕአዴግ ሥርዓት ለውጠ በምትኩ ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ የሆነን ሥርዓት ለማምጣት የሚቻለው፤ አደጋ ያደረሰውን የጎጠኝነት የጥፋት መርህ መልሶ በማራገብና አንድነትን በመሸርሸር፤ ወይም ደግሞ በውጭ ሃይሎች ድጋፍ ላይ ሙሉ ዕምነትን ጥሎ የራስን ወገኖች በማግለል ሳይሆን፤

***በዕኩልነት ላይ የተመሠረተ ሃገራዊ አንድነትንና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የትግላችን አልፋና ኦሜጋ ካደረግን ብቻ እንደሆነ አስምረውበት ገልጸዋል።***

***በማስከተልም፣ በአምባገነናዊው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሙሉ ቁጥጥር ስር በሆነው የፖለቲካ ምሕዳር ውስጥ የነበሩትንና አሁንም ያሉትን የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማሕበራት ህልውና በተመለከተ ባግባቡ ተደራጅተው ለመብታቸው እንዳይታገሉም ሆነ በ1997ቱ ምርጫ ወቅት እንደታየውና ለሥርዓቱም አማራጭ ሆነው ወደ አደባባይ እንዳይወጡ አከታትሎ ባወጣቸው ህጎች በመተብተብና በፖሊስ ሃይሉም ዕመቃ በመጠቀም አጠቃላዩን እንቅሥቃሴ ያመከነው መሆኑን፤ የ2002ቱ ምርጫ ያሳየን ውጤትም ደግሞ "ካሮትና ዱላ" የገዢውን ቡድን ፓርቲ በጠቀመ መንገድ ተቀናጅተው እንዲሠሩ የተደረገበትና የዓለም-አቀፍ ሕብረተሰብም ጭምር የታዘበው፤ የተቻውና አምባገነንነትን አጠቃልሎ በመለስ ዜናዊ ቡድን እጅ ውስጥ ያስገባ ዕውነታም እንደነበር አብራርተዋል።***

***ይህ አልበቃ ብሎም "በአገር አጀንዳ" ተጀቡኖ ስደተኛው መሐል በመግባት ተቃዋሚውን ለመከፋፈል ገዢው ቡድን ያደረጋቸውንና እያደረጋቸው ያሉትን መፍጨርጨሮች አንስተው ስደተኛው ለዚህ ሤራ መቸነፍም፤ መንበርከክም እንዳማይኖርበት፤ ይልቁንም የአገራችንን ሉዓላዊነትና የወደፊት ህልውና ጥያቄ ውስጥ እያስገባ ያለውን ገዢ ቡድን የኢትዮጵያን መሬት ለባዕድ የመቸርቸር ፖሊሲ እንድንቃወም፤ በቀረንም አንድና አንድ ብቻ የሆነ አማራጭ፤ ማለትም በአንድነት ዙሪያ፤ አጥብቀን እንድንሠራ በማሳሰብ፡ "ተቃዋሚ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ሲቪክ ማሕበራትና አገር ወዳድ ግለሰቦች ይህን አገር-አቀፉን የማሰባሰብ ጥረት እንዲደግፉ፤ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና አገራዊ አንድነት የተቀበሉ፤ ገዢው ሥርዓት መለወጥ አለበት ብለው የሚያምኑና ለዚህም በተግባር የተሠለፉ፤ እርስ በርስም ላለመጠላለፍ ተማምነው በአገራችን በኢትዮጵያ ወደፊት ለሚፈጠረው የመድበለ-ፓርቲ ሥርዓት አጥብቀው ለመሥራት የተዘጋጁ ሃይሎችን በግምባር ቀደም በሚያሳትፍ መልኩ ወደፊት የሚፈጠረው ሕብረት አካልም እንዲሆኑ በድርጅቴ ስም ጥሪ እያቀረብኩ፤ በዚህና በመሣሰሉት ጉዳዮች ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎችንም በጥያቄና መልሱ ክፍለ ጊዜ አስተናግዳለሁ" በማለት ቃል ገብተው ንግግራቸውን ቋጭተዋል።***



***ዶ/ር ወንድሙ መኮንን***

***ከዚያም በመቀጠል፤ የታጋዩን ትውልድ ገድል ጭምር እያጣቀሱና የታዳሚውን ስሜት እየቀሰቀሱ ሠፊ ንግግር ያደረጉት ዶ/ር ወንድሙ መኮንን ሲሆኑ፤ እሳቸውም ንግግራቸውን የጀመሩት ከዚህ በፊት***

ለረጅም ጊዜ ያላዩዋቸውንና አሁን እዚህ ያገኟቸውን ግለሰቦች ስም በመጥቀስና ይህም መሆን የቻለው አትላንቲክን ተሻግረው ወደካናዳ በማቅናታቸው እንደሆነ አመላክተው፤ ይህንንም አጋጣሚ በመጠቀም አገር ጥለዋቸው የተሰደዱትን ወገኖቻቸውን ደግሞ እንዲሁ ለማግኘት ያላቸው ጉጉት አማልሏቸው፡ “ቀይ ባሕርን ማን በሻገረኝ፤ አዲስ ላይ ጉዳይ ነበረኝ” በማለትና የውስጥ ስሜታቸውንና ልባቸውን እየበላ ያለውን ዕውነታ በመግለጽ ነበር።

ዶ/ር ወንድሙ ወደ ንግግራቸው አጀንዳም በመግባት በወቅቱ አጅግ አነጋጋሪ ስለሆነው የኢትዮጵያ መሬት ችብቸባ ታሪካዊ ማመሣከሪያ እንዲሆናቸው አሰብ በነሡልጣን ኢብራሂም በ1869 ገደማ ለጣልያኖች እንዴት እንደተሸጠችና ጣሊያንም ቀይቶ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለመድፈር እንዴት እንደበቃ ባጭሩ ከገለጹ በሁዋላ፤ አሁን እየተደረገ ያለው የመሬት ችብቸባ ከዚህ ቢበልጥ እንጂ የማይተናነስ ችግር በአገራችን ላይ ወደፊት ሊፈጥር እንደሚችል፤ የሕዝባችንን አሳዛኝና የሰቆቃ ኑሮ ደግሞ አስመልክቶ በችግሩና በችጋሩ ብዛት አሁን ወገኖቻችን፤ ለምነው የሚበሉ ብቻ ሳይሆን ለምነው ወላጆቻቸውን የሚያበሉ ህጻናት ጭምር፤ የሚልሱት የሚቀምሱት አጥተው ህይወታቸውን ለማቆየት ብቻ በየቆሻሻ መጣያው የተጣለ ምግብ ሲቃርሙ ማየት ሊፈጥር የሚችለውን ህሊናዊ ሰቆቃና በሕዝቡ ውስጥ የፈጠረውን የጥቃት ስሜት የሚያነሣውንና “በፈረቃ” የሚለውን ቪዲዮ በማሳየትና ይህንንም በማብራራት ላፍታም ቢሆን የታዳሚውን ህሊና በአርምሞ ወዳገር መልሰው ቀላቅለውታል። ይህንንም ሰቆቃ ስንመለከት ራሱን በእሳት አቃጥሎ በመሰዋት ለቱኒዚያ ህዝብ መነሳሳትና ለውጥ መምጣት ካበቃው የነጻነት ሰማዕት ዕውነታ እንደማይለይ ገልጸዋል።

በዚህ ስብሰባ እንዲገኙ ያደረጋቸውን ዋነኛ ዓላማም በተመለከተ ዶ/ር ወንድሙ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ፡ “ዛሬ እዚህ የተገኘሁት ትናንት እናቶቻችንና አባቶቻችን የውጭ ወራሪ ሲወርረን ያደርጉት የነበረውን ዓይነት የክተት ጥሪ ይዤ ነው። ይኸ ጥሪ ለሲቪክ ማሕበራት፤ ለፖለቲካ ድርጅቶችና ለታዋቂ ግለሰቦች የተሠነዘረና የኢትዮጵያን ዕምባ ለማድረቅ የተደረገ የክተት ጥሪ ነው። እኔ መልዕክተኛቸው ነኝ። እኛ ህብረት መሥርተናል አላልንም፤ የፈጠርነውም የህብረት ግምባር ለመፍጠር የሚያስችል ሠፊና ሁሉን የሚያሳትፍ መድረክ ብቻ ነው። አሁን በቪዲዮ እንደምታዩትም የመድረኩ መጠሪያ “ሁሉን አቀፍ ጉባዔ አዘጋጅ ኮሚቴ ለአንድነት ግንባር ምሥረታ” የሚል ነው። በዚህ አገራዊ ራዕይ ዙሪያም እንዲሰባሰቡ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሲቪክ ማሕበራት እንዲሁም ታዋቂ ግለሰቦች እንዲተባበሩን በመጠየቅ ከመስከረም እስካሁን አራት ጥሪዎችን አድርገናል። ይህ መድረክ ልዩነቶቻችንን በግልጽ አውጥተን እንድንጋገርበትና መላም እንድናበጅለት፤ በምንስማማባቸው የጋራ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ ስምምነቶችን ለመፍጠርና በሚቋቋመውም ግምባር የየበኩላችንን ድርሻ ተረክበን ለመወጣት ዕድል ይሰጠናል የሚለው የአዘጋጆቹ ጽኑ ዕምነት ቢሆንም ለዚህ ጥሪያችን ግን በተቃዋሚነት ከተሠለፉት ወገኖች ውስጥ አንዳንዶቹ እስካሁን አመርቂ ምላሽ ሊሰጡን አልቻሉም ወይም ፈቃደኞች አልሆኑም። ለመሆኑ ለዚህ ጥሪ ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ እንዳንሰጥ፤ ወያኔ ካደረሰብንና እንዳንተማመንም ካደረገን ሃገራዊ በደል ባሻገር፤ ምን የተሻለ ተስፋና አማራጭ አግኝተን ነው ወደሁዋላ እያልን ያለነው? እስከመቼስ ነው በዚህ አቋማችን የምንቀጥለው? ስንጠየቅስ ለሕዝባችንስ የምንሰጠው ምላሽ ምን ይሆናል? እነዚህና እነዚህን የመሣሰሉ ጥያቄዎችን ህዝቡ ራሱ እያነሳ መልስ እንዲሰጥባቸው እንሻለን።

“ይህ በእንዲህ እያለ”፤ ይላሉ ዶ/ር ወንድሙ፤ “በማሰባሰብ ጥረቱና ለተደጋጋሚ ጥሪያዎቻችንም ተገቢውን ምላሽ በመስጠት አብረውን እየሠሩ ያሉ ብዙ ወገኖች አሉ። ‘ክርስቶስ ለሥጋው አደላ’ የሚለው መትበሃል ባንተም ላይ ሠርቷል ካላላችሁኝ ባሁኑ ወቅት የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል ስላልሆንኩኝና ባመዛኙም በሲቪክ እንቅስቃሴው ውስጥ ግምባር ቀደም ሚና ስለምጫወት ለነዚህ ስብስቦች ያለኝ አመለካከት ግልጽ ነው። ሲቪክ ማህበራት በህዝቡ ትግል ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፤ ከማንኛውም የፖለቲካ ጥያቄ በፊትም በሰብዓዊና በዴሞክራሲያዊ መብት ዙሪያ ከፍተኛ የሆነና ከፖለቲካ ድርጅቶች የማይተናነስ ሚና ሲጫወቱ የቆዩና ያሉ ስብስቦች በመሆናቸው እነዚህን

ወገኖች ያልጨመረ ማንኛውም ዓይነት ግምባር እንደማይሰክን ያለኝ ዕምነት ጽኑ ነው።" ስለዚህም ነው በአሰባሳቢው ግብረ-ሃይል ጥሪት ብዙ የሲቪክ ማሕበራትን ለመድረስና ድጋፋቸውን ለማግኘት የተቻለው። በዚህም ጥረታችን በዓለም ዙሪያ ተመስርተው በመንቀሳቀስ ላይ ካሉት (በስም የጠቀሷቸው የሲቪክ ማሕበራት)፤ እንደ ህብረት (ኢዴሃህ)ና ከመሣሰሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና አንዳንድ ታዋቂ ግለሰቦች ጋር ስምምነት በመፍጠር የጥረቱ አካል እንዲሆኑ አድርገናል። ከሌሎች ድርጅቶችና የሲቪክ ስብሰቦችም ጋር ቀጣይ ውይይቶችን በማድረግ ላይ እንገኛለን። ከዚህ በተረፈ ግን ከእኛ ጋር ከጅምሩ ጀምሮ ሲሠራ የቆየውና አሁንም አብሮን እየሠራ ያለው ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ሲሆን ይህም ድርጅት ቅን አባላቱን በጥረቱ በማሣተፍና ይህ ዛሬ የተደረገውንም ዓይነት ስብሰባ በማዘጋጀት ጭምር ለንቅናቄያችን ከፍተኛ አስተዋጽዖ እያደረገ ይገኛል።

ኢሕአፓ የሚለውን ስም ካነሳሁ ዘንዳ፤ ይላሉ ዶ/ር ወንድሙ፤ የእኔም የቀድሞ ታሪክ መሠረት ስለሆነ ድርጅቱ ለፍትህና ለዴሞክራሲ ሲታገል የከፈለውን ከፍተኛ መስዋዕትነት በዚህ አጋጣሚ ማስታወስ እገደዳለሁ። መልሶም አንድ ሆኖ ማየት እሻለሁ፤ ለሁለት መከፈል የማይገባውና በኢትዮጵያዊነቱም ጥያቄ የማይነሳበት ይህ ድርጅት፤ ምናልባትም "ለሁለት መከፈሉ ለእኛ በጅቶናል" የሚሉትን የህወሀት/ኢሕአዴግና ሌሎች ወገኖችን ዓላማ ላለማሳካት፤ እንደገና አንድ ሆነው የአንድነቱን ጎራ እንዲያጠናክሩ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ በማለትና የዚህም የቀድሞ ድርጅታቸው ታሪክና የመስዋዕትነት ገድል ገፍቷቸው ነው መሰል፤ "የትግሉ ነው ህይወቴን" እስከመዘመርና ታሪኩን የሚጋሩ ወገኖችንም እስከማስለቀስ የደረሱበትም አጋጣሚ ነበር።

በመጨረሻም ዶ/ር ወንድሙ - ይህ ሁሉን አቀፍ አዘጋጅ ኮሚቴ ለህብረት ግምባር ምሥረታ - ዝግጅቱ እንደተጠናቀቀ በቅርቡ አንድ ሠፊ ያለና ታሪካዊም የሆነ የፖለቲካ ድርጅቶችን፤ የሲቪክ ማሕበራትንና ታዋቂ ግለሰቦችን ያካተተ ኮንፈረንስ ለመጥራት ዕቅድ እንዳለው አስታውቀው፤ በማሰባሰቡ ቀጣይ ጥረት ደግሞ እስካሁን ያልተካተቱና አመርቂ መልስም ያልሰጡትን እንደ ግንቦት-7ና ኢሕአፓ የመሣሰሉትን ሕብረ-ብሔር ድርጅቶችና ሌሎችም የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ሃይሎችን ወደስብሰቡ ለማምጣት ጥረቱ እንደሚቀጥል በመናገር ንግግራቸውን ቋጭተዋል።

ሦስተኛውና የመጨረሻው እንግዳ ተናጋሪ የነበሩት ደግሞ ዶ/ር ቡሻ ታዓ ሲሆኑ፤ ዶ/ር ቡሻም በተናጋሪነት የተጋበዙት **የኢትዮጵያውያን ማሕበር በቶሮንቶና አካባቢውን** ለረጅም ጊዜ በፕሬዚደንትነት ያገለገሉ የማሕበረሰብ መሪ በመሆናቸውና ማሕበራቸውም በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች ዙሪያ ከተቃዋሚው ጎን በተደጋጋሚ ተሠልፎ ድምጹን እንዲያሰማ ወሳኝ ሚና ከተጫወቱት የቦርድ አባላት አንዱ በመሆናቸው ነው። ዶ/ር ቡሻ በመድረኩ ተገኝተው ታዳሚውን ያወያዩበት ርዕስም ባመዛኙ በኢትዮጵያ ወቅታዊ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ በዴሞክራሲና በእኩልነት ጥያቄ ዙሪያ ሲሆን፤ በነዚህም ስም ስለተደረጉትና እየተደረጉ ስላሉት የህወሀት/ኢሕአዴግ የፖለቲካና የህግ ሸፍጦች አንድ ባንድ በማንሳት ነበር ያወያዩት። ለውይይታቸውም መነሻ ያደረጉት የዴሞክራሲን፤ የሕግንና የማሕበራዊ ፍትህን ንድፈ-ሃሳባዊ ምንጮችና ርዕዮታዊ መሠረቶችን ከአፍላቂዎቻቸው አመለካከት አኳያ በመተንተንና ከአገሪቱ ተጨባጭ ዕውነታም ጋር በማወዳደር/በማሣከር ነበር።

የፍትህንና የዴሞክራሲን መተከሎች ርዕዮታዊ መሠረትም እንደ ዋቢ አድርገው ያቀረቡት እንደ ሩሶና የመሣሰሉትን ፈላስፎችና ሶሲዎሎጂስቶች አመለካከት አንተርሰው ሲሆን፤ ከነዚህም ሶሲዎሎጂስቶች ትንታኔ አኳያ ወያኔ/ኢሕአዴግ በምንም መልኩ ፍትሐዊም ዴሞክራሲያዊም ሊሆን እንደማይችል ይገልጻሉ። ባንዳንድ ወገኖች ዙሪያም በብዛት እየተነገረ እንደምሰማው ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ስለመጥፋቱ ወይም ስለመቀልበሱ ነው። የእኔ ጥያቄ ደግሞ ዴሞክራሲ ለመሆኑ በኢትዮጵያ መቼ ገብቶ ነው ጠፋም/ተቀለበሰ የሚባለው? ይሆናል። ዴሞክራሲ እኮ በወታደር፤ በጎጠኛና በመሣሰሉት ወገኖች የሚሰጥም፤ በነርሱ የበላይነት የሚዳብርም ዕውነታ አይደለም። የዴሞክራሲ መሠረቱ ሕዝብ ነው፤ ህዝብ መጀመሪያ መብቱ ተክብሮለት በነጻ ይሁንታ የሰጠው የፖለቲካ ሥርዓት ካለ ብቻ ነው

ዴሞክራሲ አለ የሚባለው። ለዴሞክራሲ መኖር ምልክት የሚሰጡን ሁኔታዎች፤ ሂዩመን ራይትስ ዎችና ሌሎችም በሰፋት እንደጻፋለት፤ የህግ የበላይነት መኖር፣ የህግ አስከባሪዎች ከፖለቲካ በላይ/ነጻ መሆንና የመሣሰሉት ሊኖሩ ከቻሉ ነው። የአገሪቱ ሠራዊትም ቢሆን ሥልጣኑን ከያዘው ፓርቲ ነጻ መሆን ይገባዋል። ይህ ሁኔታ ዛሬ በኢትዮጵያ የለም። የዜጎች መብትንም ሆነ እኩልነት በተግባር ማዋልም፤ ማክበርም ሲቻል ነው ዴሞክራሲ አለ ማለት የሚቻለው። ስለ እኩልነትም ጽንሰ-ሃሳብ ከሊብራል ርዕዮት አኳያ ሲተነትኑ፤ ዶ/ር ቡሻ እንዲህ ብለው ያብራራሉ፤ "እኩልነት ሲባል የፍላጎት እኩልነት፤ የችሎታ እኩልነትና የንብረት እኩልነት ሳይሆን፤ በመብት፤ በዴሞክራሲና በህግ ዙሪያ መኖር ስለሚገባው እኩልነት"፤ እንደሆነ አስምረውበት ነው።

የወያኔን ሕገ-መንግሥት ስንመረምር ደግሞ፤ ምንም እንኳ ሕገ-መንግሥቱ በጽንሰ-ሃሳብ ደረጃ ብዙም እንከን የማይወጣለት መስሎ ቢታይም፤ በአፈጻጸም ደረጃ ግን (ለምሣሌ አንቀጽ 39) በተግባር ላይ የሚውሉት ሕገ-መንግሥቱን ተከትለው የወጡ ህጎችና አዋጆች (ለምሳሌ የሲቪክ ማሕበራት መቆጣጠሪያ ህግ)ና የመሣሰሉት ሲሆኑ፤ ሕገ-መግሥቱም ራሱ ቢሆን በ1997ቱ ምርጫና ከዚያም በሁዋላ እንደታየው በፍርድ ቤቶች ጭምር ተጣምሞ ሲተረጎምና በፖሊስ ሃይልም ሲሻር እንደቆየና አሁንም ቢሆን የህዝቡን መብት ከማስከበር አኳያ ዋጋ እንደሌለው ገልጸዋል። በዚህም የተነሳ ብዙ ወገኖቻችን ያላግባብ ለመታገት ስለመብቃታቸው፤ ያለፍትህ ስለመገደላቸው፤ አገር ለቅቀው ስለመሰደዳቸው፤ አገርም እየተቆረሰች፤ ለባዕድ እየተቸበቸበችና ሉዓላዊነቷም እየተደፈረ ያለችበትን ሁኔታ በዝርዝር በመግለጽ ንግግራቸውን ደምድመዋል።

በመጨረሻም የጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜ ሆኖ ከታዳማዊዎች *(ስብሰባውን ከመጀመሪያ አስከመጨረሻ በኢንተርኔት እያስተላለፉ ከነበሩት ከቪ-ኢ-ዲ-አር አበራሽ በርታና ከቃሌ ፓል ቶክ ታዳሚዎች ጭምር)* እጅግ ጠቃሚና አነጋጋሪ የሆኑ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተሠንዝረው ለጥያቄዎቹ መልስ ተሰጥቶባቸዋል። ከተነሱት ጥያቄዎችም ውስጥ ጥቂቶቹ፦

1) የተከፋፈለው ኢሕአፓ ለምን እንደገና አንድ አይሆንም?
2) ባለፈው ሣምንት በዚሁ ከተማ ስብሰባ ተደርጎ ነበር፤ ዛሬ ደግሞ እናንተ አደረጋችሁ፤ የዚህ ዓይነቱ ፉክክር ለምን አስፈለገ?
3) አገር ቤት ያለው ወጣት የትግል እንቅስቃሴውን የተወው ይመስላል፤ ምክንያቱ ምን ይመስላችሁዋል? ህወሀትና አሕአዴግ የምንለውን ስያሜ በተመለከተ ለያየተን ማየት ያለብን ይመስለኛል። ህወሃት የነመለስ ዜናዊ ድርጅት ነው። የዚያም ድርጅት አባል የሚሆኑት እነማን እንደሆኑ እናውቃለን። ብዙ ሰው ለመኖር ሲል የኢሕአዴግ አባል ሆኖ ካርድ ወስዷል። ወገኖቻችንን እንዳናሸሽ ሁለቱን ነጣጥለን መመልከት አይኖርብንም ወይ?
4) ኢትዮጵያዊ የምንለው ማነው?
5) ኦነግ እንደሚባለው ሳይሆን፤ የተወሰነውም ክፍል ቢሆን፤ የኦሮሞ ህዝብ ድጋፍ አለው። ባገር ቤት መድረክ የብሔር ድርጅቶችን ይዞ ለመጓዝ የሁለት ቋንቋ ፖሊሲ በተግባር አውሏል፤ እናንተስ ይህን በተግባር ማዋል ይገዳችሁዋልን? የሚሉና የመሣሰሉ ነበሩ።

ጥያቄዎቹን በተመለከተ ሁሉም አወያዮች ጠያቂዎቹ ባመዛኙ የረኩባቸውን መልሶች ሰጥተዋል። የመጀመሪያውን ጥያቄ በተመለከተ ግን የዕለቱ ሰብሳቢና የኢሕአፓ (ዴ) አመራር አባል የሆኑት አቶ ለይኩን ተሾመ ከሌላው የኢሕአፓ ቡድን ጋር ለመቀራረብና መልሶም ለመወሃድ የኢሕአፓ (ዴ) አባላት በጉባዔ ጭምር ተወያየተውበትና አምነውበት የመገናኘቱን ጥረት የሚያደርግ ኮሚቴም ጭምር ተፈጥሮ ላለፉት ሦስት ዓመታት ጥረቶች እንደተረጉና አሁንም እየተደረጉ እንዳሉ ገልጸዋል።

ከተራ ቁጥር 2 እስከ 5 የተመለከቱትን ጥያቄዎች ደግሞ ከተሰጡት መልሶች አኳያ አጠር ባለ መልኩ ነጥብ በነጥብ እናቀርባለን።

- በእኛ በኩል ፋክክር የሚሉት ነገር የለም፤ የእኛ ስብሰባ የተጠራው ባካባቢው በጊዜ መቀራረብ ሌላ ስብሰባ ባልታቀደበት ወቅት ነው። ማንም ያድርገው ማን በሀገር ጉዳይ ላይ የሚደረግን ማንኛውንም ስብሰባ እንደግፋለን፤ ከቻልንም እንገኛለን።
- የአገር ቤቱ ወጣት እጁን አጣጥፎ የተቀመጠ አይመስለኝም፤ ይልቁንስ ችግሩ ያለው እዚህ በስደት ላይ ይመስለኛል። በመቀጠልም፤ ዶ/ር ወንድሙ ሲያብራሩ፤ "ያገር ቤቱ ወጣት አሁንም ቢሆን ስልታዊ በሆነ መንገድ ለቀጣዩ ትግል እየተዘጋጀ ይገኛል፤ ይታገላልም" በማለት መልስ ሰጥተዋል። ህወሃት-ኢሕአዴግ የሚሉት የስም ልዩነት የፖለቲካ አቋም ልዩነት አይመስለኝም፤ ይሉና ዶ/ር ቡሻ በመቀጠል፡ "ኢሕአዴግ የሚለውን ቃል በቅርበት ስንተነትን፤ የምናገኘው የህወሃት ካባ ወይም ጓንት ሆኖ ብቻ ነው።"
- "በእኔ ዕምነት ኢትዮጵያዊ ማነው የሚለው ጥያቄ ባመዛኙ የዜግነት መግለጫ ስለሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ የተወለዱትንና በእናታቸው ወይም በአባታቸው ወይም በሁለቱም ወገን ያሉትን ወገኖቻችንን ማንነት ይገልጻል"፤ ሲሉ ዶ/ር ወንድሙ መልሰዋል።
- በመጨረሻም የተነሳውን ጥያቄ በተመለከተ ዶ/ር ወንድሙ ሲመልሱ ከኦነግም ሆነ ከሌሎች የብሔር ድርጅቶች ጋር የሚለያየን ቋንቋ ሳይሆን በአገር አንድነት ዙሪያ ባሉ ጥያቄዎች ላይ ነው። በጸረ-ኢሕአዴግ ግምባር ከነርሱም ጋር ቢሆን መሰለፍ አያዳግተንም፤ ግና ጸረ-ኢሕዴግ መሆን ብቻ ራሱ በቂ አይደለም። ከዚያ የማይተናነሱና ሲሆንም የሚበልጡ የአገር አንድነት ጥያቄዎች፤ የአገር ሉዓላዊነት ጥያቄዎች፤ የዴሞክራሲና ፍትህ ጥያቄዎች በቅድሚያ ሊያስማሙን ይገባል። በዚህ ዙሪያ ገና ብዙ ሥራ ይጠብቀናል። ደግሞስ አገሪቱ ለመሆኑ ሁለት ቋንቋ ብቻ ነው ያላት? ስማኒያ ብሔረሰቦች ባሏት አገርስ ውስጥ ሁለት ቋንቋ ቀርቶ ከዚያስ በላይ መናገር እንዳንችል የሚያግደን ምን ሊኖር ይችላል? ችግሩ ከፊታችን የተጋረጠው አጥፊ ቡድን ሆኖ ነው እንጂ። ስለዚህም ቁምነገሩ "ከፈረሱ በፊት ጋሪውን" አለማስቀደሙ ላይ ይመስለኛል በማለት መልሰው እንዳጠናቀቁ፤ ዶ/ር ቡሻም በማከል፡ "በድረ-ገጽ ጭምር የሚታየውን የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን ሳይለውጡ አደባባይ ወጥቶና ከአንድነት ሃይሎች ጋር ቆሞ ኢትዮጵያዊ ነኝ፤ ጸረ-ወያኔ ነኝ፤ ብሎ መናገር ብቻውን በቂ አይደለም። ለመታመን ይህንን መሠረታዊ ለውጥ አስቀድሞ ማምጣት ያስፈልጋል" ሲሉ መልሰዋል። አቶ መሥፍን ተፈራም በፕሮግራሙ እንደተመለከተው ድርጅታቸው ኢሕአፓ (ዴ) ስለሚከተለው ግልጽ ፖሊሲና ከኦነግም ጋር ለመቀራረብ ስለተደረጉት ጥረቶች አንዳንድ ነጥቦችን አክለው የጥያቄና መልሱ ክፍለ ጊዜ በዚህ አብቅቷል።

በመጨረሻም የትግሉ አንጋፋ ከሆኑት ታዳሚዎች ውስጥ አቶ ተሻገር ብርሃኔ በ2004 የጻፉትን ግጥም በማንበብ የታዳሚውን ስሜት አነሳስተዋል። የዕለቱ ስብሰባም ከመዘጋቱ በፊት ታዳሚዎች ከስብሰባው አዳራሽ እንደወጡ ወደ ላሊበላ ሬስቶራንት በማምራት በተዘጋጀው የራት ግብዣና የጠረቤዛ ዙሪያ ውይይት ላይ እንዲሣተፉ ሰብሳቢው ጥሪ አድርገው የዕለቱ ስብሰባ አብቅቷል። በተዘጋጀውም ምሽት ላይ ከ 40 በላይ የሆኑ እንግዶች ተገኝተው እስከ ምሽቱ 11፡00PM ውይይቱና ጭውውቱ ቀጥሎ በዚህ መልኩ ተጠናቋል።

**ቶሮንቶ፤ ግንቦት 9 ቀን 2003 (May 17, 2011)**